BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## የግል መረጃን መጠየቅ
## ወንድሞች ወይም እህቶችስ አሉህ/አሉሽ?

*This is not a word-for-word transcript.*

ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊተዋቸው የማይቻላቸውን የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation በደህና መጡ። ሐና እባላለሁ። በዚህ ክፍል ሰዎች ወንድሞች ወይንም እህቶች እንዳሏቸው ወይንም እንደሌሏቸው እንዴት መጠየቅ እንደሚቻል ይማራሉ።
እስኪ ሁለት ሰዎች ወንድሞች ወይንም እህቶች መኖር ያለመኖራቸውን ሲነጋገሩ ያዳምጡ።

**Tina**
*Have you got any brothers or sisters?*

**John**
*Yes, I've got two sisters. How about you?*

**Tina**
*I've got a brother.*

ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን። በመጀመሪያ ቲና ጆንን 'ወንድሞች ወይንም እህቶች አሉህ ወይ' 'Have you got any brothers or sisters?' ስትል ነው የጠየቀችው። አስታውሱ ሁሌም 'have you got…'. ብለን ስንጠይቅ 'any' የሚለውን ቃል አብረን እንጠቀማለን። ያዳምጡና ሐረጉን ይድገሙ።

**Insert**
*Have you got any brothers or sisters?*
*Have you got any brothers or sisters?*

ከዚያ ጆን 'ሁለት እህቶች አሉኝ' 'I've got two sisters.' በማለት መልሷል። 'I've got' እና 'I have' ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው። እናም ደግሞ ከአንድ በላይ እህት ሲኖረን 'sister' በሚለው ቃል ላይ 'S' ን እንጨምራለን። ነገር ግን አንድ እህት ብቻ ከሆነ ያለን በ 'sister' ላይ 'S'ን አንጨምርም። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

**Insert**
*Yes, I've got two sisters.*
*Yes, I've got two sisters.*

ከዚያም ጆን 'አንቺስ?' 'How about you?' በማለት ተመሳሳዩን ጥያቄ አዙሮ ጠይቋታል። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

**Insert**
*How about you?*
*How about you?*

ከዚያም ቲና 'አንድ ወንድም አለኝ' 'I've got a brother.' ብላ መለሰች። 'a brother' ማለት 'አንድ ወንድም' ማለት ነው። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

***Insert***
*I’ve got a brother.*
*I’ve got a brother.*

በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች ምን ያህል ወንድሞች እና እህቶች እንዳሏቸው ሲጠየቁ በማዳመጥ እርስዎ ሲሉ የቆዩቱን ይፈትሹ።

*Have you got any brothers or sisters?*

*Yes, I’ve got a sister. How about you?*

*I’ve got two brothers and a sister.*

*Have you got any brothers or sisters?*

*Yes, I’ve got a sister and a brother. How about you?*

*I’ve got two sisters.*

*Have you got any brothers or sisters?*

*Yes, I’ve got two brothers. How about you?*

*I’ve got two sisters and a brother.*

በጣም  ግሩም! እስኪ እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*ወንድሞች ወይንም እህቶች አሉህ?*
*Have you got any brothers or sisters?*

*አዎ፥ ሁለት እህቶች አሉኝ።*
*Yes, I’ve got two sisters.*

*አንችስ?*
*How about you?*

*አንድ ወንድም አለኝ።*
*I’ve got a brother.*

በጣም ጥሩ፤ እስኪ አሁን የዛሬዎቹን አገላለፆች ለማስተዋል ሙሉውን ውይይት ያዳምጡ።

***Tina***
*Have you got any brothers or sisters?*


© British Broadcasting Corporation 2018

***John***
*Yes, I've got two sisters. How about you?*

***Tina***
*I've got a brother.*

በጣም ጥሩ! አሁን በእንግሊዝኛ ሰዎች ምን ያህል ወንድሞች እና እህቶች እንዳሏቸው መጠየቅ ይችላሉ። የተማሩትን ነገር መለማመድን አይዘንጉ። ጓደኛ ይፈለጉና ምን ያህል ወንድሞች እና እህቶች እንዳሏቸው በእንግሊዝኛ በመጠየቅ ልምምድ ያድርጉ። ለተጨማሪ የዕለት ተዕለት እንግሊዝኛ በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። ደህና ይሁኑ! Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018